አትግደሉ!

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩህ፥ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው።

17÷33 *"ያቺንም አላህ እርም ያረጋትን ነፍስ ያለ ሕግ አትግደሉ"*። وَلَا تَقْتُلُوا النَّفْسَ الَّتِي حَرَّمَ اللَّهُ إِلَّا بِالْحَقِّ

"ዘንበ" ذَنب ማለት "ኃጢአት" ማለት ነው፥ በሥነ-ኃጢአት ጥናት"hamartiology" ውስጥ "ኃጢአት" ማለት "አሏህ ያዘዘውን መልካም ነገር አለማድረግ፥ የከለከለውን ክፉ ነገር ማድረግ" ማለት ነው። ኃጢአት "ከባኢሩ አዝ-ዘንብ" ذَنب كَبَائِر እና "ሶጋኢሩ አዝ-ዘንብ" ذَنب صَغَائِر ተብለው ለሁለት ይከፈላሉ፥ "ከባኢር" كَبَائِر ማለት "ዐበይ" "ታላቅ" ማለት ሲሆን "ሶጋኢር" صَغَائِر ማለት ደግሞ "ንዑስ" "ትንሽ" ማለት ነው። ከዐበይት ኃጢአቶች መካከል አንዱ ነፍስን ያለ ሕግ መግደል ነው፦

ኢማም ቡኻርይ መጽሐፍ 83, ሐዲስ 53

ዐብደሏህ ኢብኑ ዐምሪው እንደተረከው፦ "ነቢዩም" ﷺ" አሉ፦ *"ዐበይት ኃጢአቶች በአሏህ ላይ ማሻረክ፣ ወላጆችን አለማክበር፣ ነፍስን መግደል እና የውሸት መሓላ ናቸው"*። عَنْ عَبْدِ اللَّهِ بْنِ عَمْرٍو، عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم قَالَ " الْكَبَائِرُ الإِشْرَاكُ بِاللَّهِ، وَعُقُوقُ الْوَالِدَيْنِ، وَقَتْلُ النَّفْسِ، وَالْيَمِينُ الْغَمُوسُ ."

"ቀትሉ አን-ነፍሥ" قَتْلُ النَّفْس የሚለው ቃል ይሰመርበት! አምላካችን አሏህ ነፍስን መግደል ሐራም አርጓል፦
17÷33 *"ያቺንም አላህ እርም ያረጋትን ነፍስ ያለ ሕግ አትግደሉ"*። وَلَا تَقْتُلُوا النَّفْسَ الَّتِي حَرَّمَ اللَّهُ إِلَّا بِالْحَقِّ

"እርም ያረጋት" ለሚለው የገባው ቃል "ሐረመ" حَرَّمَ መሆኑ እንባቢ ልብ ይለዋል። "ሐራም" حَرَام የሚለው ቃል እራሱ "ሐረመ" حَرَّمَ ማለትም "ከለከለ" ከሚል ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን "የተከለከለ" ማለት ነው። እንደውም ያለጥፋት አንድን ሰው መግደል ሰዎችን ሁሉ እንደገደለ ነው፦
5÷32 *"በዚህ ምክንያት በእስራኤል ልጆች ላይ እነሆ ያለ ነፍስ መግደል ወይም በምድር ላይ ያለማጥፋት ካልሆነ በስተቀር ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፥ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው"* ማለትን ጻፍን። مِنْ أَجْلِ ذَٰلِكَ كَتَبْنَا عَلَىٰ بَنِي إِسْرَائِيلَ أَنَّهُ مَن قَتَلَ نَفْسًا بِغَيْرِ نَفْسٍ أَوْ فَسَادٍ فِي الْأَرْضِ فَكَأَنَّمَا قَتَلَ النَّاسَ جَمِيعًا وَمَنْ أَحْيَاهَا فَكَأَنَّمَا أَحْيَا النَّاسَ جَمِيعًا
አንድን ነፍስ ያለ ሕግ መግደል እርሱ አግብቶ ቤተሰብ፣ ነገድ፣ ጎሳ፣ አገር እያለ ሕዝብ የሚሆንበትን የተፈጥሮ ዐላማና ዒላማ መቅጨት ስለሆነ ነፍስ ያለ ሕግ የገደለ ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው። የአር-ረሕማንም ባሮች ያችንም አሏህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለ ቂሷስ ሕግ የማይገድሉ ናቸው፥ ነገር ግን ያችንም አሏህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለ ቂሷስ ሕግ በመግደል ይህንንም የሚሠራ ሰው ከዱንያ ፍርድ ቢያመልጥ በአኺራ ከአሏህ ቅጣትን ያገኛል፦
25÷68 *"እነዚያም ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ የማይገዙት፣ ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለ ሕግ የማይገድሉት፣ የማያመነዝሩትም ናቸው። ይህንንም የሚሠራ ሰው ቅጣትን ያገኛል"*። وَالَّذِينَ لَا يَدْعُونَ مَعَ اللَّهِ إِلَـٰهًا آخَرَ وَلَا يَقْتُلُونَ النَّفْسَ الَّتِي حَرَّمَ اللَّهُ إِلَّا بِالْحَقِّ وَلَا يَزْنُونَ ۚ وَمَن يَفْعَلْ ذَٰلِكَ يَلْقَ أَثَامًا

ቅሉ ግን ወሰን አልፈው የሚገሉትን ሰዎች መግደል ቂሷስ ነው÷ “ቂሷስ” قِصَاص የሚለው ቃል “ቋሰ” قَاصَّ ማለትም “አመሳሰለ” ከሚል ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን “ማመሳሰል” ማለት ነው። ሰው ጤናማ ሕይወት ይኖር ዘንድ አምላካችን አሏህ ቂሷስን ደንግጓል፦

2÷179 *”ባለ አእምሮዎች ሆይ! ለእናንተም በማመሳሰል ሕግ ውስጥ ሕይወት አለላችሁ። ትጠነቀቁ ዘንድ ገዳይን መግደል ተደነገገላችሁ”*። وَلَكُمْ فِي الْقِصَاصِ حَيَاةٌ يَا أُولِي الْأَلْبَابِ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ

"ገዳይን መግደል" ሐላል ነው÷ እዚህ አንቀጽ ላይ “ማመሳሰል” ለሚለው ቃል የገባው “ቂሷስ” قِصَاص መሆኑ አንባቢ ልብ ይለዋል። ቂሷስ ወሰን በታለፈበት ላይ ወሰን ያለፈውን ብጤውን ወሰን ማለፍ ነው፦

2÷194 *”የተከበረው ወር በተከበረው ወር አንጻር ነው። ሑሩማት ሁሉ ቂሷስ ናቸው÷ በእናንተም ላይ ወሰን ያለፈባችሁን ሰው በእናንተ ላይ ወሰን ባለፈው ብጤ በእርሱ ላይ ወሰን እለፉበት። አላህንም ፍሩ አላህ ከሚፈሩት ጋር መኾኑንም ዕወቁ”*። الشَّهْرُ الْحَرَامُ بِالشَّهْرِ الْحَرَامِ وَالْحُرُمَاتُ قِصَاصٌ ۚ فَمَنِ اعْتَدَىٰ عَلَيْكُمْ فَاعْتَدُوا عَلَيْهِ بِمِثْلِ مَا اعْتَدَىٰ عَلَيْكُمْ ۚ وَاتَّقُوا اللَّهَ وَاعْلَمُوا أَنَّ اللَّهَ مَعَ الْمُتَّقِينَ

"በእናንተ ላይ ወሰን ባለፈው ብጤ በእርሱ ላይ ወሰን እለፉበት" የሚለው ኃይለ-ቃል ይሰመርበት! እነዚህን የሚጋደሉ ሰዎች መጋደል ፍትሓዊ ነው፦

2÷190 *እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን በአላህ መንገድ ተጋደሉ። ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎን አይወድምና*። وَقَاتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ الَّذِينَ يُقَاتِلُونَكُمْ وَلَا تَعْتَدُوا ۚ إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ الْمُعْتَدِينَ

2÷193 *ሁከት እስከማይገኝ እና ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሉዋቸው። ቢከለክሉም ወሰንን ማለፍ በበዳዮች ላይ እንጂ የለም ወሰን አትለፉባቸው*። وَقَاتِلُوهُمْ حَتَّىٰ لَا تَكُونَ فِتْنَةٌ وَيَكُونَ الدِّينُ لِلَّهِ ۖ فَإِنِ انتَهَوْا فَلَا عُدْوَانَ إِلَّا عَلَى الظَّالِمِينَ

አሏህ ወሰን አላፊዎን አይወድም÷ ወሰን የሚያልፉት በዳዮች ናቸው። ከመጋደል የሚከለከሉትን ወሰን አይታለፍም÷ ከዚህ ውጪ ወሰን ታልፎባቸው ለእነዚያ ለሚገደሉት ምእመናን እነርሱ የተበደሉ በመኾናቸው መጋደል ተፈቀደላቸው፦

22÷39 *”ለእነዚያ ለሚገደሉት ምእመናን እነርሱ የተበደሉ በመኾናቸው መጋደል ተፈቀደላቸው። አላህም እነርሱን በመርዳት ላይ በእርግጥ ቻይ ነው”*። أُذِنَ لِلَّذِينَ يُقَاتَلُونَ بِأَنَّهُمْ ظُلِمُوا ۚ وَإِنَّ اللَّهَ عَلَىٰ نَصْرِهِمْ لَقَدِيرٌ

"በሕግ ቢሆን እንጂ" ማለት እንደዚህ ነው÷ ወሰን አልፎ የሚመጣውን በዳይ ሁሉ ጂሃዱል ዐመሊያህ በመጠቀም መጋደል ሐላል ነው።

ምዕራፍ አንድ

ነቢያችን"ﷺ" እንደ ጎርጎሮሳውያን አቆጣጠር በ 610 ድኅረ-ልደት የተውሒድ አንኳር የሆነውን “ላ ኢላህ ኢልለሏህ” لَا إِلَٰهَ إِلَّا اللَّهُ ካወጁ በኃላ የመካ ሙሽሪኮች እሳቸውን ሊያስሩ ወይም ሊገድሉ አሊያም ከመካህ ሊያስወጡ ተማከሩባቸው።
8÷30 *"እነዚያም የካዱት ሊያስሩህ ወይም ሊገድሉህ ወይም ከመካ ሊያወጡህ በአንተ ላይ ”በመከሩብህ” ጊዜ አስታውስ"*።** **وَإِذْ يَمْكُرُ بِكَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لِيُثْبِتُوكَ أَوْ يَقْتُلُوكَ أَوْ يُخْرِجُوكَ**

ከዚያም የመካ ሙሽሪኮች እርሳቸውን እና ባልደረቦቻቸው ከመካህ ወደ መዲናህ በ 622 ድኅረ-ልደት አሳደዷቸው÷ የመካ ሙሽሪኮች በደል በዚህ አላበቃ ብሎ መዲናህ ድረስ መጥተው መግደል ጀመሩ። አምላካችን አሏህም ለምእመናን መጋደልን ፈቀደላቸው።
22÷39 *”ለእነዚያ ለሚገደሉት ምእመናን እነርሱ የተበደሉ በመኾናቸው መጋደል ተፈቀደላቸው። አላህም እነርሱን በመርዳት ላይ በእርግጥ ቻይ ነው”*። أُذِنَ لِلَّذِينَ يُقَاتَلُونَ بِأَنَّهُمْ ظُلِمُوا ۚ وَإِنَّ اللَّهَ عَلَىٰ نَصْرِهِمْ لَقَدِيرٌ
22÷40 *"ለእነዚያ «ጌታችን አላህ ነው» ከማለታቸው በስተቀር ያለ አግባብ ከአገራቸው የተባረሩ ለሆኑት ተፈቀደ"*። الَّذِينَ أُخْرِجُوا مِن دِيَارِهِم بِغَيْرِ حَقٍّ إِلَّا أَن يَقُولُوا رَبُّنَا اللَّهُ

ያለ አግባብ ከአገራቸው ለተባረሩት ምእመናን መጋደል ከተፈቀደ በኃላ በ 624 ድኅረ-ልደት በበድር ዘመቻ አምላካችን አሏህ፦ "እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን በአላህ መንገድ ተጋደሉ" የሚል አንቀጽ አወረደ።
2÷190 *እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን በአላህ መንገድ ተጋደሉ። ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎን አይወድምና*። وَقَاتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ الَّذِينَ يُقَاتِلُونَكُمْ وَلَا تَعْتَدُوا ۚ إِنَّ اللَّهَ لَا يُحِبُّ الْمُعْتَدِينَ

"እነዚያ" የሚል አመልካች ተውላጠ-ስም የሚያመለክተው ወሰን አልፈው የሚጋደሉትን የመካህ ሙሽሪኮች ነው÷ አንድ ምእመን መጋደል ያለበት ለክብሩ፣ ለዘሩ፣ ለብሔሩ፣ ለፓለቲካ አቋሙ ሳይሆን ለአሏህ ብሎ መሆን ስላለበት "በአላህ መንገድ" የሚል መርሕ በአጽንዖትና በአንክሮት ያስቀምጣል። ዐውደ-ንባቡ ላይ "ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው" የሚለው ከመካ ያወጧቸውን የመካ ሙሽሪኮች ስለሆነ "ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው" የሚል ኃይለ-ቃል አለ።
2÷191 *"ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው! ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው!* وَاقْتُلُوهُمْ حَيْثُ ثَقِفْتُمُوهُمْ وَأَخْرِجُوهُم مِّنْ حَيْثُ أَخْرَجُوكُمْ

የአንድን አንቀጽ ዐረፍተ-ነገሩን ከዐውዱ አያይዞ መረዳት "ፊቲሆት”exegesis” ሲሆን ብዙ ጊዜ የሚሸነሪዎች ችግር የአንድን አንቀጽ ዐረፍተ-ነገሩን ከዐውዱ አፋቶ በመረዳት “ሰጊጎት”Eisegesis” ማድረግ ነው። ሐረጉ ይቀጥልና፦ "መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት። በተከበረው መስጊድም ዘንድ በእርሱ ውስጥ እስከሚጋደሉዋችሁ ድረስ አትጋደሉዋቸው። ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው! የከሓዲዎች ቅጣት እንደዚህ ነው" ይላል፦
2÷191 *"መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት። በተከበረው መስጊድም ዘንድ በእርሱ ውስጥ እስከሚጋደሉዋችሁ ድረስ አትጋደሉዋቸው። ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው! የከሓዲዎች ቅጣት እንደዚህ ነው"*። وَالْفِتْنَةُ أَشَدُّ مِنَ الْقَتْلِ ۚ وَلَا تُقَاتِلُوهُمْ عِندَ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ حَتَّىٰ يُقَاتِلُوكُمْ فِيهِ ۖ فَإِن قَاتَلُوكُمْ فَاقْتُلُوهُمْ ۗ كَذَٰلِكَ جَزَاءُ الْكَافِرِينَ

“አል-መሥጂዱል ሐረም” الْمَسْجِدِ الْحَرَام መካህ ውስጥ የሚገኘው ከዕባህ ሲሆን እዛ ቦታ "እስከሚጋደሉዋችሁ ድረስ አትጋደሉዋቸው! ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው" ተብሏል።
ከመበደል እና ከመጋደል ቢከለከሉ አሏህ መሓሪ ነውና ወሰን አትለፉባቸው፦
2÷192 *"ቢከለከሉም አላህ መሓሪ አዛኝ ነው"*። فَإِنِ انتَهَوْا فَإِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ
2÷193 *"ቢከለክሉም ወሰንን ማለፍ በበዳዮች ላይ እንጂ የለም ወሰን አትለፉባቸው*። فَإِنِ انتَهَوْا فَلَا عُدْوَانَ إِلَّا عَلَى الظَّالِمِينَ

ቅሉ ግን ወሰን አልፈው እነዚያ በሃይማኖት ከሚጋደሉት፣ ከቤት ከሚያስወጡት፣ በማስወጣትም በሚረዱት በዳዮች ላይ ወሰን ማለፍ ሐላል ነው፦
60÷9 አላህ የሚከለክላችሁ ከእነዚያ በሃይማኖት ከተጋደሉዋችሁ፣ ከቤቶቻችሁም ካወጡዋችሁ፣ እናንተም በማውጣት ላይ ከረዱት ከሓዲዎች እንዳትወዳጁዋቸው ብቻ ነው። إِنَّمَا يَنْهَاكُمُ اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ قَاتَلُوكُمْ فِي الدِّينِ وَأَخْرَجُوكُم مِّن دِيَارِكُمْ وَظَاهَرُوا عَلَىٰ إِخْرَاجِكُمْ أَن تَوَلَّوْهُمْ

በተቃራኒው ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሉት እና ከአገሮች ካላወጡት ከሓዲዎች መልካም መዋዋል እና ወደ እነርሱ ማስተካከል አሏህ አይከለክልም፦ አምላካችን አሏህ አስተካካዮችን ይወዳል፦
60÷8 *"ከእነዚያ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጡዋችሁ ከሓዲዎች መልካም ብትውሉላቸው እና ወደ እነርሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም። አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና"*። لَّا يَنْهَاكُمُ اللَّهُ عَنِ الَّذِينَ لَمْ يُقَاتِلُوكُمْ فِي الدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُم مِّن دِيَارِكُمْ أَن تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوا إِلَيْهِمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُقْسِطِينَ

ምዕራፍ ሁለት

ሑሩማት ሁሉ ቂሷስ ናቸው፥ በእናንተም ላይ ወሰን ያለፈባችሁን ሰው በእርሱ ላይ ወሰን እለፉበት። አሏህንም ፍሩ! አሏህ ከሚፈሩት ጋር መኾኑንም ዕወቁ፦

2፥194 *"የተከበረው ወር በተከበረው ወር አንጻር ነው። ሑሩማት ሁሉ ቂሷስ ናቸው፥ በእናንተም ላይ ወሰን ያለፈባችሁን ሰው በእናንተ ላይ ወሰን ባለፈው ብጤ በእርሱ ላይ ወሰን እለፉበት። አላህንም ፍሩ! አላህ ከሚፈሩት ጋር መኾኑንም ዕወቁ"*። **الشَّهْرُ الْحَرَامُ بِالشَّهْرِ الْحَرَامِ وَالْحُرُمَاتُ قِصَاصٌ ۚ فَمَنِ اعْتَدَىٰ عَلَيْكُمْ فَاعْتَدُوا عَلَيْهِ بِمِثْلِ مَا اعْتَدَىٰ عَلَيْكُمْ ۚ وَاتَّقُوا اللَّهَ وَاعْلَمُوا أَنَّ اللَّهَ مَعَ الْمُتَّقِينَ**

"ሙተቂን" مُتَّقِين ማለት "አሏህን የሚፈሩ" ማለት ነው፥ አሏህ የሚፈራ ሰው የሰውን ሐቅ በመንካት ወሰን አያልፍም፥ ወሰን ባለፈው ብጤ በእርሱ ላይ ወሰን ማለት ግን ሐላል ነው። የተከበረው ወር በተከበረው ወር አንጻር ነው፥ የወሮች ቁጥር አሏህ ዘንድ ዐሥራ ሁለት ወር ናቸው። ከእነርሱ አራቱ የተከበሩ ወሮች ዙል-ቀዒዳህ፣ ዙል-ሒጃህ፣ ሙሐረም እና ረጀብ ናቸው፦

9፥36 *የወሮች ቁጥር አላህ ዘንድ በአላህ መጽሐፍ ውስጥ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረበት ቀን ዐሥራ ሁለት ወር ነው። ከእነርሱ አራቱ የተከበሩ ናቸው*። إِنَّ عِدَّةَ الشُّهُورِ عِندَ اللَّهِ اثْنَا عَشَرَ شَهْرًا فِي كِتَابِ اللَّهِ يَوْمَ خَلَقَ السَّمَاوَاتِ وَالْأَرْضَ مِنْهَا أَرْبَعَةٌ حُرُمٌ

ኢማም ቡኻርይ መጽሐፍ 65 ሐዲስ 4662

አቡበክር"ረ.ዐ" እንደተረከው፦ ነቢዩም"ﷺ" አሉ፦ *"ዘመን አላህ ሰማያትን እና ምድር በፈጠረበት ቀን የቀድሞ ሁኔታ ይመለሳል። አንድ ዓመት ዐሥራ ሁለት ወር ነው፥ ከእነርሱም አራቱ የተከበሩ ናቸው። ሦስቱ ተከታታይ ዙል-ቀዒዳህ፣ ዙል-ሒጃህ፣ ሙሐረም ናቸው፥ አራተኛው በጀማዱ-ሣኒ እና በሻዕባን መካከል ያለው ረጀብ ነው*። عَنْ أَبِي بَكْرَةَ، عَنِ النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم قَالَ " إِنَّ الزَّمَانَ قَدِ اسْتَدَارَ كَهَيْئَتِهِ يَوْمَ خَلَقَ اللَّهُ السَّمَوَاتِ وَالأَرْضَ، السَّنَةُ اثْنَا عَشَرَ شَهْرًا مِنْهَا، أَرْبَعَةٌ حُرُمٌ، ثَلاَثٌ مُتَوَالِيَاتٌ، ذُو الْقَعْدَةِ وَذُو الْحِجَّةِ وَالْمُحَرَّمُ وَرَجَبُ مُضَرَ الَّذِي بَيْنَ جُمَادَى وَشَعْبَانَ

የመካ አጋሪዎችን የመታገሻ ጊዜ የተከበሩ ወሮች ዙል-ቀዒዳህ፣ ዙል-ሒጃህ፣ ሙሐረም እና ረጀብ ተሰኟቸዋል፥ በዚህ የጊዜ ገደብ ካልተከለከሉ እነዚህ የተከበሩ ወሮች ባለቁ ጊዜ "በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው" ተባለ፦

9፥5 *"የተከበሩትም ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን በአገኛችሁባቸው ስፍራ ግደሉዋቸው"*። فَإِذَا انسَلَخَ الْأَشْهُرُ الْحُرُمُ فَاقْتُلُوا الْمُشْرِكِينَ حَيْثُ

የመካ አጋሪዎች ከሙሐጅሮች ጋር አንዳቸው ለአንዳቸው ላይ ጦር በድጋሚ እንዳይከፍት በሚል የስምምነት ኪዳን ነበራቸው፦

9፥1 *"ይህች ከአላህ እና ከመልክተኛው ወደ እነዚያ ቃል ኪዳን ወደ ተጋባችኋቸው አጋሪዎች የምትደርስ ንጽሕና ናት"*። بَرَاءَةٌ مِّنَ اللَّهِ وَرَسُولِهِ إِلَى الَّذِينَ عَاهَدتُّم مِّنَ الْمُشْرِكِينَ

ይህንን ውል አፍርሰው ወደ ጦርነት ሲገቡ ውሉን የሚያድሰብት አራት የተከበሩ ወሮች ተሰጣቸው፥ ከቃል ኪዳንን በኃላ መሐላን በማፍረስ፣ ሃይማኖትን በማነወር እና ትንኮሳውን በመጀመራቸው በተገኙበት እንዲገደሉ ታዘዙ፦

9፥12 *"ከቃል ኪዳናቸው በኃላ መሐላዎቻቸውን ቢያፈርሱ፣ ሃይማኖታችሁንም ቢያነውሩ፣ የክህደት መሪዎችን ከክህደት ይከለከሉ ዘንድ ተዋጉዋቸው። እነርሱ ቃል ኪዳን የላቸውምና"*። وَإِن نَّكَثُوا أَيْمَانَهُم مِّن بَعْدِ عَهْدِهِمْ وَطَعَنُوا فِي دِينِكُمْ فَقَاتِلُوا أَئِمَّةَ الْكُفْرِ ۙ إِنَّهُمْ لَا أَيْمَانَ لَهُمْ لَعَلَّهُمْ يَنتَهُونَ

9፥13 *"መሐላዎቻቸውን ያፈረሱትን መልክተኛውንም ለማውጣት ያሰቡትን ሕዝቦች እነርሱ ለመጀመሪያ ጊዜ የጀመሩዋችሁ ሲኾኑ ለምን አትዋጉዋቸውም? ትፈሩዋቸዋላችሁን? ምእምናን እንደ ኾናችሁም አላህ ይበልጥ ልትፈሩት የተገባው ነው"*። أَلَا تُقَاتِلُونَ قَوْمًا نَّكَثُوا أَيْمَانَهُمْ وَهَمُّوا بِإِخْرَاجِ الرَّسُولِ وَهُم بَدَءُوكُمْ أَوَّلَ مَرَّةٍ ۚ أَتَخْشَوْنَهُمْ ۚ فَاللَّهُ أَحَقُّ أَن تَخْشَوْهُ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ

ከአጋሪዎቹ እነዚያ ቃል ኪዳን ምንም ያላጎደሉት እና አንድንም ያልረዱትን ግን እስከ ህልፈተ ሕይወታቸው ሳይነኩ ይኖራሉ፦

9÷4 *"ከአጋሪዎቹ እነዚያ ቃል ኪዳን የተጋባችኋቸው እና ከዚያም ምንም ያላጎደሉባችሁ በእናንተ ላይም አንድንም ያልረዱባችሁ ሲቀሩ፤ እነዚህን ቃል ኪዳናቸውን እስከ ጊዜያቸው መጨረሻ ሙሉላቸው። አላህ ጥንቁቆችን ይወዳልና"*። إِلَّا الَّذِينَ عَاهَدتُّم مِّنَ الْمُشْرِكِينَ ثُمَّ لَمْ يَنقُصُوكُمْ شَيْئًا وَلَمْ يُظَاهِرُوا عَلَيْكُمْ أَحَدًا فَأَتِمُّوا إِلَيْهِمْ عَهْدَهُمْ إِلَىٰ مُدَّتِهِمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُتَّقِينَ

"አሏህ የምሠራውን ያየኛል፣ የምናገረውን ይሰማኛል፣ የማስበውን ያውቅብኛል" ብለው የሚፈሩትን ሙተቂን ባሮቹን ይወዳል፥ እነዚያ በአል-መሥጂዱል ሐረም ዘንድ ቃል ኪዳን የተጋቡት ሙሽሪኮች በውሉ መሠረት ቀጥ እስካሉ ድረስ ሳይነኩ ቀጥ ተብሎላቸዋል፦

9÷7 *"ለአጋሪዎቹ አላህ ዘንድ እና እመልክተኛው ዘንድ ቃል ኪዳን እንዴት ይኖራቸዋል? እነዚያ በተከበረው መስጊድ ዘንድ ቃል ኪዳን የተጋባችኋቸው ብቻ ሲቀሩ። እነዚህ በቃል ኪዳናቸው ለእናንተ ቀጥ እስካሉላችሁ ድረስ ለእነርሱም ቀጥ በሉላቸው። አላህ ጥንቁቆችን ይወዳልና"*። كَيْفَ يَكُونُ لِلْمُشْرِكِينَ عَهْدٌ عِندَ اللَّهِ وَعِندَ رَسُولِهِ إِلَّا الَّذِينَ عَاهَدتُّمْ عِندَ الْمَسْجِدِ الْحَرَامِ ۖ فَمَا اسْتَقَامُوا لَكُمْ فَاسْتَقِيمُوا لَهُمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ يُحِبُّ الْمُتَّقِينَ

በአናቅጽ ማብቂያ ላይ፦ "አላህንም ፍሩ! አላህ ከሚፈሩት ጋር መኾኑንም ዕወቁ" "ምእምናን እንደ ኾናችሁም አላህ ይበልጥ ልትፈሩት የተገባው ነው" "አላህ ጥንቁቆችን ይወዳልና" መባሉ በራሱ ጂሃዱል ዐመሊያህ ከነፍሚያህ ባሻገር ለሊሏሂ ተብሎ የሚደረግ ጅሁድ መሆኑን አመላካች ነው። በጦርነቱ የተማረኩ እና የተከበቡ መጠባበቅ በየመንገዱ ይደረግላቸዋል፥ ይህም ወደ አሏህ በተውባህ መጥተው ሶላትንም በደንቡ ቢሰግዱ፣ ግዴታ ምጽዋትንም ቢሰጡ መንገድ ይለቀቅላቸዋል። ያንን ካደረጉ የሃይማኖት ወንድሞቻችሁ ናቸው፦

9÷5 *"ያዙዋቸውም፣ ክበቡዋቸውም፣ ለእነርሱም መጠባበቅ በየመንገዱ ተቀመጡ። ቢጸጸቱም፣ ሶላትንም በደንቡ ቢሰግዱ፣ ግዴታ ምጽዋትንም ቢሰጡ መንገዳቸውን ልቀቁላቸው። አላህ መሓሪ አዛኝ ነውና"*። وَجَدتُّمُوهُمْ وَخُذُوهُمْ وَاحْصُرُوهُمْ وَاقْعُدُوا لَهُمْ كُلَّ مَرْصَدٍ ۚ فَإِن تَابُوا وَأَقَامُوا الصَّلَاةَ وَآتَوُا الزَّكَاةَ فَخَلُّوا سَبِيلَهُمْ ۚ إِنَّ اللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ

9÷11 *"ቢጸጸቱም፣ ሶላትንም ቢሰግዱ፣ ዘካንም ቢሰጡ የሃይማኖት ወንድሞቻችሁ ናቸው። ለሚያውቁ ሕዝቦችም አንቀጾችን እናብራራለን"*። فَإِن تَابُوا وَأَقَامُوا الصَّلَاةَ وَآتَوُا الزَّكَاةَ فَإِخْوَانُكُمْ فِي الدِّينِ ۗ وَنُفَصِّلُ الْآيَاتِ لِقَوْمٍ يَعْلَمُونَ

አንድ ምርኮኛ በፍልሚያው ወቅት ሳይሠልም ተማርኮ ጥገኝነት"Asylum" ቢጠይቅ ምንም ሳይነካ የአሏህን ንግግር እስኪሰማ ዘንድ ጥገኝነት ይሰጠዋል፥ ጥበቃ እንዲደረግለት ወደ መጠበቂያው ስፍራ ይወሰዳል፦

9÷6 *"ከአጋሪዎችም አንዱ ጥገኝነትን ቢጠይቅ የአላህን ንግግር እስኪሰማ ዘንድ አስጠጋው! ከዚያም ወደ መጠበቂያው ስፍራ አድርሰው። ይህ እነርሱ የማያውቁ ሕዝቦች በመኾናቸው ነው"*። وَإِنْ أَحَدٌ مِّنَ الْمُشْرِكِينَ اسْتَجَارَكَ فَأَجِرْهُ حَتَّىٰ يَسْمَعَ كَلَامَ اللَّهِ ثُمَّ أَبْلِغْهُ مَأْمَنَهُ ۚ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ قَوْمٌ لَّا يَعْلَمُونَ

ምርኮኛው የአሏህን ንግግር ከቃሪው ሲሰማ ልቡ የመማረክ አጋጣሚ ስላለው ማሰማቱ ጥሩ የሂዳያህ ሰበብ ነው።

ምዕራፍ ሦስት

ዓለም እስኪሰማና እስኪስማማ ድረስ ጂሃድ በሐቅ እና በባጢል መካከል ያለ ትግል ነው፥ እስከ ፍርዱ ቀን ድረስ እውነት ለማንገሥ ሐሠትን ለማርከሥ መጋደል "ፈርዱል ኪፋያህ" فَرْض الكِفَايَة ማለትም "የጥቅል ግዴታ" ነው፦

2፥193 *"وَقَاتِلُوهُمْ حَتَّىٰ لَا تَكُونَ فِتْنَةٌ وَيَكُونَ الدِّينُ لِلَّهِ"*።

አንቀጹን ልብ ብለነው ከሆነ "ተጋደሉ" እንጂ "ግደሉ" አይልም። ልዩነቱን እስቲ እንመልከት፦

4፥84 *"በአላህም መንገድ ተጋደል"*። فَقَاتِلْ فِي سَبِيلِ اللَّهِ

2፥244 *"በአላህም መንገድ ተጋደሉ"*። وَقَاتِلُوا فِي سَبِيلِ اللَّهِ

እነዚህ አናቅጽ ላይ "ተጋደል" ለሚለው የገባው ቃል "ቃቲል" قَاتِلْ ሲሆን "ተጋደሉ" ለሚለው ደግሞ "ቃቲሉ" قَاتِلُوا ነው። "ግደል" ለማለት ቢሆን ኖሮ "ኡቅቱል" اقْتُلْ ሲሆን "ግደሉ" ለማለት ደግሞ "ኡቅቱሉ" اقْتُلُوا ይሆን ነበር፥ ተጨማሪ አንድ አንቀጽ እንመልከት፦

9፥111 *"በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ፣ ይገድላሉ፣ ይገደላሉ"*። يُقَاتِلُونَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ فَيَقْتُلُونَ وَيُقْتَلُونَ

አያችሁ? "ይጋደላሉ" ለሚለው የገባው ቃል "ዩቃቲሉነ" يُقَاتِلُونَ ሲሆን "ይገድላሉ" ለሚለው ግን "የቅቱሉነ" يَقْتُلُونَ ነው። "ቀትል" قَتْل ማለትም "መግደል" እና "ቂታል" قِتَال ማለትም "ገድል" ሁለት ለየቅል ቃላት እና ትርጉም አላቸው፥ ስለዚህ "መጋደል" ወይም "ገድል" ማለት ጂሃዱል ቀልቢያህ፣ ጂሃዱል ቀውሊያህ እና ጂሃዱል ዐመሊያህ ተጠቅሞ የአሏህን ንግግር የበላይ ማድረግ ነው፦

ኢማም ቡኻርይ መጽሐፍ 3, ሐዲስ 65

አቡ ሙሣ እንደተረከው፦ "አንድ ሰው ወደ ነቢዩ"ﷺ" መጥቶ፦ *"የአሏህ መልእክተኛ ሆይ! የትኛው መጋደል ነው በአሏህ መንገድ መጋደል? ከእኛ መካከል በቁጣውና በንዴት ምክንያት የሚጋደል አለ፥ አንዳንዱ ለኩራትና ለንዴት የሚጋደል አለ" ብሎ ጠየቀ። እርሳቸውም ወደ እርሱ ከፍ ብለው፦ "የአሏህ ንግግር የበላይ ለማድረግ የሚጋደል እርሱ ነው በአሏህ መንገድ የሚጋደል" ብለው መለሱለት"*። عَنْ أَبِي مُوسَى، قَالَ جَاءَ رَجُلٌ إِلَى النَّبِيِّ صلى الله عليه وسلم فَقَالَ يَا رَسُولَ اللَّهِ، مَا الْقِتَالُ فِي سَبِيلِ اللَّهِ فَإِنَّ أَحَدَنَا يُقَاتِلُ غَضَبًا، وَيُقَاتِلُ حَمِيَّةً. فَرَفَعَ إِلَيْهِ رَأْسَهُ ـ قَالَ وَمَا رَفَعَ إِلَيْهِ رَأْسَهُ إِلاَّ أَنَّهُ كَانَ قَائِمًا ـ فَقَالَ " مَنْ قَاتَلَ لِتَكُونَ كَلِمَةُ اللَّهِ هِيَ الْعُلْيَا فَهُوَ فِي سَبِيلِ اللَّهِ عَزَّ وَجَلَّ

ሁከት እስከማይገኝ እና ሃይማኖት ለአሏህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ከኩፋሮች ጋር እንጋደላለን፥ ዓለም በአሏህ ሸሪዓህ እስክትደዳደር ድረስ መጋደሉ ይቀጥላል። ተወዳጁ ነቢያችን"ﷺ" የታዘዙበት መርሕ ይህ ነው፦

ኢማም ቡኻርይ መጽሐፍ 3 ሐዲስ 18

ኢብኑ ዑመር እንደተረከው፦ የአሏህ መልእክተኛም"ﷺ" እንዲህ አሉ፦ "ሰዎችን "ከአሏህ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ አለመኖሩን እና ሙሐመድም የአሏህ መልእክተኛ ነው" ብለው እስኪመሰክሩ፣ ሶላትን እስኪቆሙ እና ዘካህን እስኪያወጡ ድረስ እንድጋደላቸው ታዝዣለሁ"*። عَنِ ابْنِ عُمَرَ، أَنَّ رَسُولَ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم قَالَ " أُمِرْتُ أَنْ أُقَاتِلَ النَّاسَ حَتَّى يَشْهَدُوا أَنْ لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ وَأَنَّ مُحَمَّدًا رَسُولُ اللَّهِ، وَيُقِيمُوا الصَّلاَةَ، وَيُؤْتُوا الزَّكَاةَ

እዚህም ሐዲስ ላይ "አን ኡቃቲለ" أَنْ أُقَاتِلَ ማለትም "እንድጋደል" የሚል ቃል እንጂ "አን አቅቱለ" أَنْ أَقْتُلَ ማለትም "እንድገድል" የሚል ቃል የለም። ገድል አጠቃላይ ሦስቱንም የጂሃድ ክፍል የሚይዝ ቃል ነው።

ሪያዱ አስ-ሷሊሒን መጽሐፍ 1, ሐዲስ 184

አቢ ሠዒድ አል-ኹድሪይ"ረ.ዐ." እንደተረከው፦ "የአሏህ መልእክተኛ"ﷺ" እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ፦ *"ከእናንተ ውስጥ እኩይ ነገር ያየ በእጁ ይቀይረው፣ ካልቻለ በምላሱ ያውግዝ፣ ይህንንም ካልቻለ በልቡ ይጥላው። በልብ መጥላት ደካማው ኢማን ነው"*። عن أبي سعيد الخدري رضي الله عنه قال: سمعت رسول الله صلى الله عليه وسلم يقول: "من رأى الخد منكرًا فليغيره بيده ، فإن لم يستطع فبلسانه، فإن لم يستطع فبقلبه وذلك أضعف الإيمان

በእጅ፣ በምላስ እና በልቡ ያልታገለ የጎመንዘር ያህል ኢማን የለውም። ምእምናን ማለት በገንዘቦቻቸው እና በነፍሶቻቸውም በአሏህ መንገድ የታገሉት ብቻ ናቸው፦ እነዚያ እነርሱ እውነተኞቹ ናቸው። አሏህ እኛን ውርደት ያከናነበን ከጂሃድ በመራቃችን ነው፦

49፦15 *ምእምናን እነዚያ በአላህ እና በመልእክተኛው ያመኑት ከዚያም ያልተጠራጠሩት "በገንዘቦቻቸው እና በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ የታገሉት ብቻ ናቸው"። እነዚያ እነርሱ እውነተኞቹ ናቸው*። إِنَّمَا الْمُؤْمِنُونَ الَّذِينَ آمَنُوا بِاللَّهِ وَرَسُولِهِ ثُمَّ لَمْ يَرْتَابُوا وَجَاهَدُوا بِأَمْوَالِهِمْ وَأَنفُسِهِمْ فِي سَبِيلِ اللَّهِ ۚ أُولَٰئِكَ هُمُ الصَّادِقُونَ

ሡነን አቢ ዳውድ መጽሐፍ 24, ሐዲስ 47

ኢብኑ ዑመር"ረ.ዐ." እንደተረከው፦ የአሏህ መልእክተኛ"ﷺ" እንዲህ አሉ፦ *"በሪባ በተገበያያቹህ ጊዜ፣ ኩበቶችን በተከትላችሁ ጊዜ፣ እርሻኝ በወዳዳቹህ ጊዜ እና ጂሃድን በተዋቹህ ጊዜ አሏህ ውርደት ያከናንባችኃል፦ ይህንንም ውርደት ወደ ዲናቹህ እስካልተመለሳቹህ ድረስ ከእናንተ አያነሳም"*። عَنِ ابْنِ عُمَرَ، قَالَ سَمِعْتُ رَسُولَ اللَّهِ صلى الله عليه وسلم يَقُولُ " إِذَا تَبَايَعْتُمْ بِالْعِينَةِ وَأَخَذْتُمْ أَذْنَابَ الْبَقَرِ وَرَضِيتُمْ بِالزَّرْعِ وَتَرَكْتُمُ الْجِهَادَ سَلَّطَ اللَّهُ عَلَيْكُمْ ذُلاًّ لاَ يَنْزِعُهُ حَتَّى تَرْجِعُوا إِلَى دِينِكُمْ

ምዕራፍ አራት

9÷29 *"እነዚያን በአላህ እና በመጨረሻዉ ቀን የማያምኑትን፣ አላህ እና መልክተኛዉ እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትን እና "ከ"እነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እዉነተኛዉንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ሆነዉ ግብርን በእጅቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተጋደሏቸው"*። قَٰتِلُواْ ٱلَّذِينَ لَا يُؤۡمِنُونَ بِٱللَّهِ وَلَا بِٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ وَلَا يُحَرِّمُونَ مَا حَرَّمَ ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥ وَلَا يَدِينُونَ دِينَ ٱلۡحَقِّ مِنَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ حَتَّىٰ يُعۡطُواْ ٱلۡجِزۡيَةَ عَن يَدٖ وَهُمۡ صَٰغِرُونَ

"አህሉል ኪታብ " أَهْلُ الْكِتَابِ ማለት "የመጽሐፉ ሰዎች" ማለት ሲሆን ክርስቲያኖች እና አይሁዳውያን ናቸው÷ ከአህሉል ኪታብ ጋር መልካም በሆነች ሙግት እንጂ አትሟገቱ÷
29÷46 *"የመጽሐፉን ባለቤቶችም በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ። ከእነርሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር"*። وَلَا تُجَادِلُوا أَهْلَ الْكِتَابِ إِلَّا بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ إِلَّا الَّذِينَ ظَلَمُوا مِنْهُمْ

"እነዚያን የበደሉት" የተባሉት ከአህሉል ኪታብ መካከል ዕውር ድንብር ጸለምተኛ አመለካከል ያላቸው ናቸው÷ ወደ እኛ የተወረደው ቁርኣን እና ወደ እነርሱ የተወረደው የትምህርቱ ጭብጥ ተውሒድ ስለሆነ "አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው" በሉ! ተብሏል÷
29÷46 *"በሉም «በዚያ ወደ እኛ በተወረደው ወደ እናንተም በተወረደው አመንን። አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው። እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን"*።» وَلَا تُجَادِلُوا أَهْلَ الْكِتَابِ إِلَّا بِالَّتِي هِيَ أَحْسَنُ إِلَّا الَّذِينَ ظَلَمُوا مِنْهُمْۖ وَقُولُوا آمَنَّا بِالَّذِي أُنزِلَ إِلَيْنَا وَأُنزِلَ إِلَيْكُمْ وَإِلَـٰهُنَا وَإِلَـٰهُكُمْ وَاحِدٌ وَنَحْنُ لَهُ مُسْلِمُونَ

ሁሉን የፈጠረ አንድ አምላክ አሏህ ብቻ ነው÷ እኛም ለእርሱ "ሙሥሊሙን" مُسْلِمُون ነን። እንግዲህ እኛ÷ "አሏህ አንድ ማንነትን እና ምንነት ነው" ብለን የምናምን ሙሥሊሙን እነርሱን የምንጣራው "አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው" የሚል ነው÷
ኢማም ቡኻሪይ መጽሐፍ 97 ሐዲስ 2
"ኢብኑ ዐባሥ እንዳስተላለፈው ነቢዩ"ﷺ" ሙዓዝን ወደ የመን በላኩ ጊዜ እንዲህ አሉ÷ *"ከመጽሐፍ ሰዎች የሆኑ ሕዝቦች ታገኛለህ። በቅድሚያ የላቀውን አሏህን አንድ ነው እንዲሉ ትጠራቸዋለህ"* ። يَقُولُ سَمِعْتُ ابْنَ عَبَّاسٍ، يَقُولُ لَمَّا بَعَثَ النَّبِيُّ صلى الله عليه وسلم مُعَاذًا نَحْوَ الْيَمَنِ قَالَ لَهُ " إِنَّكَ تَقْدَمُ عَلَى قَوْمٍ مِنْ أَهْلِ الْكِتَابِ فَلْيَكُنْ أَوَّلَ مَا تَدْعُوهُمْ إِلَى أَنْ يُوَحِّدُوا اللَّهَ تَعَالَى

እዚህ ሐዲስ ላይ "ዩወሐዱ" يُوَحِّدُوا የሚለው የግስ መደብ ይሰመርበት! " ዋሒድ" وَاحِد የሚለው ቃል "ወሐደ" وَحَّدَ ማለትም "አንድ አደረገ" ከሚል ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን "አንድ" ማለት ነው። "ተውሒድ" تَوْحِيد ማለት "አንድነት" ማለት ሲሆን አሏህ አንድ አድርጎ ከፍጡራን የመነጠሉ እሳቤ ነው÷ ይህንን እሳቤ የሚያራምድ "ሙዋሒድ" مُوَحِّد ይባላል። አህሉል ኪታብን ስናገኛቸው ቅድሚያ ወደ ተውሒድ እሳቤ እንጠራቸዋለን÷ ይህ ተውሒድ "ላ "ላ ኢላሀ ኢልለሏህ" لَا إِلَهَ إِلَّا اللَّهُ ነው÷
ኢማም ቡኻሪይ መጽሐፍ 24 ሐዲስ 1
"ኢብኑ ዐባሥ"ረ.ዐ." እንዳስተላለፈው ነቢዩ"ﷺ" ሙዓዝን"ረ.ዐ." ወደ የመን በላኩ ጊዜ እንዲህ አሉ÷ *"ከአሏህ በቀር አምላክ እንደሌለ እና እኔም የአሏህ መልእክተኛ መሆኔን እንዲመሰክሩ ጥራቸው"*። عَنِ ابْنِ عَبَّاسٍ ـ رضى الله عنهما ـ أَنَّ النَّبِيَّ صلى الله عليه وسلم بَعَثَ مُعَاذًا ـ رضى الله عنه ـ إِلَى الْيَمَنِ فَقَالَ " ادْعُهُمْ إِلَى شَهَادَةِ أَنْ لاَ إِلَهَ إِلاَّ اللَّهُ، وَأَنِّي رَسُولُ اللَّهِ

ይህንን ጥሪ ተቀብለው ከሠለሙ ይሁንና ይበል የሚያስብል ነው። ቅሉ ግን አሻፈረኝ ብለው በአሏህ እና በመጨረሻዉ ቀን ካላመኑ እንዲሁ አሏህ እና መልክተኛዉ እርም ያደረጉትንም እርም ካላደረጉ ጂዚያህ መክፈል ብቻ ይወጅብባቸዋል፦

9÷29 *"እነዚያን በአላህ እና በመጨረሻዉ ቀን የማያምኑትን፣ አላህ እና መልክተኛዉ እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትን እና "ከ"እነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡት ሰዎች እዉነተኛዉንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ሆነዉ ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተጋደሏቸው"*። قَٰتِلُواْ ٱلَّذِينَ لَا يُؤۡمِنُونَ بِٱللَّهِ وَلَا بِٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ وَلَا يُحَرِّمُونَ مَا حَرَّمَ ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥ وَلَا يَدِينُونَ دِينَ ٱلۡحَقِّ مِنَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ حَتَّىٰ يُعۡطُواْ ٱلۡجِزۡيَةَ عَن يَدٖ وَهُمۡ صَٰغِرُونَ

"ጂዝያህ" جِزْيَةَ የሚለው ቃል "ጀዛ" جَزَى ማለትም "ከፈለ" ከሚል ሥርወ-ቃል የመጣ ሲሆን "ክፍያ" ማለት ነው፦ ይህም ክፍያ "ግብር" ነው። አንቀጹ የሚለው "ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ አስልሚቸው" ሳይሆን "ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተጋደሏቸው" ነው፦ በደውለቱ አሽ-ሸሪዓህ ሥር ያሉ ምእመናን ዘካህን ግብር አርገው ሲከፍሉ አህሉል ኪታብ ደግሞ ጂዝያህን ግብር አርገው ይከፍላሉ። አንቀጹ ላይ በሃይማኖት ስለማስገደድ የሚናገርበት ሽታው የለውም፦ በተረፈ በሃይማኖት ማስገደድ ሆነ ሰዎችን አማኞች እንዲኾኑ ማስገደድ በሸሪዓችን የለም፦

2÷256 *"በሃይማኖት ማስገደድ የለም። ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ"*። لَآ إِكۡرَاهَ فِي ٱلدِّينِۖ قَد تَّبَيَّنَ ٱلرُّشۡدُ مِنَ ٱلۡغَيِّۚ

10÷99 *"ጌታህም በሻ ኖሮ በምድር ያሉት ሰዎች ሁሉም የተሰበሰቡ ሆነው ባመኑ ነበር። ታዲያ አንተ ሰዎችን አማኞች እንዲኾኑ ታስገድዳለህን?"*። وَلَوۡ شَآءَ رَبُّكَ لَأٓمَنَ مَن فِي ٱلۡأَرۡضِ كُلُّهُمۡ جَمِيعًاۚ أَفَأَنتَ تُكۡرِهُ ٱلنَّاسَ حَتَّىٰ يَكُونُواْ مُؤۡمِنِينَ

አሏህ ለሁላችንም ሂዳያህ ይስጠን! አሚን።

"""""""""""""""ተፈፀመ"""""""""""""""""

✍ከወንድም ወሒድ ዑመር
https://t.me/Wahidcom

ወሠላሙ ዐለይኩም